# የአራስ ህጻን የመስማት ችሎታ ማጣሪያ የመረጃ ሉህ

**Newborn Hearing Screening Fact Sheet — Amharic**



## የአራስ ህጻን የመስማት ችሎታ ማጣሪያ ምንድን ነው?

የአራስ ህጻን የመስማት ችሎታ ማጣሪያ ህጻናት ከመደበኛ መጠን ውጪ ያላቸውን የመስማት ችሎታ ደረጃዎች የሚያጣራ ምርመራ ነው። አራስ ህጻናት ከተወለዱ በኋላ ከደም ምልክት እና በደም ውስጥ ያለ የኦክስጅን መጠን መለካት ጋር አንድ ላይ ሊከናወኑ ከሚገቡ ሶስት ማጣሪያዎች ውስጥ አንዱ ነው።



ደም ምልክት ማጣሪያ

በደም ውስጥ ያለ የኦክስጅን መጠን ማጣሪያ

የመስማት ችሎታ ማጣሪያ

## የመስማት ችሎታ ማጣሪያ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ንግግር እና ቋንቋ ማደግ የሚጀምረው ከውልደት ጀምሮ በመሆኑ በተቻለ መጠን ማንኛውንም የመስማት ችሎታ ልዩነቶች መለየት አስፈላጊ ነው። ከመደበኛው መጠን ውጪ የመስማት ችሎታ ደረጃዎች ያለዉ ልጅ አስቀድሞ እርዳታ ካላገኘ በንግግር እና በቋንቋ ችግር ሊያጋጥመው ይችላል። አንድ ህጻን ከተለመደው መጠን ውጭ የመስማት ችሎታ ደረጃ ካለው ከእነዚህ ህጻናት ውስጥ አብዛኞቹ ከፍ ያሉ ድምጾች ስለሚያስደነግጣቸው እና የሚያዳምጡ ስለሚመስሉ ብዙውን ጊዜ ለወላጆች ወይም ለአቅራቢዎች በቀላሉ የማይታይ ነው። ከክትትል ምርመራ ጋር ማጣሪያ ከመደበኛው መጠን ውጪ የመስማት ችሎታ ደረጃዎችን ቀደም ብሎ ለማግኘት ብቸኛው መንገድ ነው። በመጀመሪያው እድሜ ላይ ልጅዎ ከመደበኛው መጠን ውጪ የሆነ የመስማት ችሎታ ደረጃዎች እንዳሉት ማወቅ እርስዎን እና ልጅዎን ለመነጋገር የተሻሉ መንገዶችን ለማግኘት የሚያግዛችሁ ይሆናል።

## የልጄ የመስማት ችሎታ እንዴት እና መቼ ይጣራል?

እንደ ትልልቅ ልጆች ወይም አዋቂዎች የመስማት ችሎታ ምርመራዎች የአራስ ህጻናት የመስማት ችሎታ ማጣሪያ ከልጅዎ ንቁ ተስትፎን አይጠይቅም። ይልቁኑም፣ ትንሽ የማጣሪያ መሳሪያ የልጅዎ የውስጠኛው የጆሮ ክፍል እና የጆሮ ነርቭ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ እየለካ እያለ ለስላሳ ድምጾችን የሚያጫውት ይሆናል። ለአራስ ህጻን የመስማት ችሎታ ማጣሪያ በአሁኑ ጊዜ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉት ሁለቱ ዘዴዎች የኦታኮስቲክ ልቀቶች (otoacoustic emissions, OAE) እና ራስሰር የኦዳማጭ የአዕምሮ ምላሽ (automated auditory brainstem response, AABR) ናቸው። ተጨማሪ ዝርዝሮችን ለማግኘት በጀርባው በኩል ይመልከቱ።

ማጣሪያው በተቻለ መጠን በፍጥነት ሊከናወን ይገባል እና ልጅዎ አንድ ወር ሳይሞላው በፊት ቢጠናቀቅ የተሻለ ነው። ልጅዎ ሆስፒታል ውስጥ ከተወለደ፣ የመጀመሪያው ማጣሪያ እርስዎ እና ልጅዎ ወደ ቤት ከመሄዳችሁ በፊት ሊከናወን ይገባል። የመስማት ችሎታ ማጣሪያ ልጅዎ በተረጋጋበት፣ በደንብ በተመገበበት እና ምቾት በሚያገኝበት ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ይከናወናል።

## ውጤቶቹ ምን ማለት ናቸው?

ልጅዎ የ አልፎአል(PASS} ውጤት ከደረሰው፣ ማጣሪያው የልጅዎ የመስማት ችሎታ በዚያን ጊዜ ጤናማ ነው ማለት ነዉ። የመስማት ችግር በአንድ ሰው ህይወት ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት ይችላል ይሁን እንጂ የመስማት ችግርን ወይም ያመለጡ የንግግር ምዕራፎችን በተመለከተ ማናቸውንም ስጋቶች ከልጅዎ አቅራቢ ጋር መወያየት አስፈላጊ ነው።

ልጅዎ REFER/አላለፈም (did not pass) የሚል ውጤት ከደረሰው፣ ማጣሪያው ልጅዎ ለንግግር እና ለቋንቋ እድገት አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉንም ድምጾች መስማቱን ለማረጋገጥ ተጨማሪ ምርመራ እንደሚያስፈልግ ያሳያል። አቅራቢዎ በተቻለ መጠን በፍጥነት ለክትትል ቀጠሮ በማዘጋጀት የሚያግዝዎት ይሆናል።

## OAE እና AABR የሚሰሩት እንዴት ነው?

በ OAE፣ በእያንዳንዱ ጆሮ ውስጥ የተቀመጠ ለስላሳ የፕላስቲክ ጫፍ ለስላሳ ድምጾችን ያደርሳል፤ እንዲሁም ጆሮው በመደበኛነት በሚሰራበት ጊዜ የሚከሰተውን የገደል ማሚቶ ይለካል። በ AABR፣ የጆሮ ማድመጫዎች የፈተና ድምጾችን ያደርሳሉ። በልጁ ጭንቅላት እና አንገት ላይ የተቀመጡት ቃኚዎች የልጁ የጆሮ ነርቭ ለእነዚያ ድምጾች እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ ይለካል። ለሁለቱም OAE እና AABR፣ ውጤቱ PASS ወይም REFER/አላለፈም መሆን ወይም አለመሆኑን ኮምፒውተሩ ይለካል።

### ቅድመ-መስማት ችሎታ ጥቁመት እና የጣልቃ መግባት ፕሮግራም

ቅድመ-መስማት ችሎታ ጥቁመት እና ጣልቃ መግባት (EHDI) ፕሮግራም አራስ ህጻናት እና ከተለመደው መጠን ውጭ የመስማት ደረጃ ያላቸው ወይም አደጋ የተጋለጡ ጨቅላ ህጻናት ለመለየት ይረዳል እንዲሁም ቤተሰቦች ተገቢውን የጣልቃመግባት አገልግሎቶች እንዲያገኙ ይመራል።

የ EHDI ፕሮግራም ግቦች ሁሉም ህጻናት የሚከተሉትን እንዲያገኙ ነው፡-

- **ከ 1 ወር እድሜ** በፊት የጆሮ የመስማት ችሎታ እንዲመረመር
- **ከ 3ወር እድሜ በፊት** የምርመራ ምዘና
- ከ 6 ወራት እድሜ በፊት የቅድመ ጣልቃገብነት አገልግሎቶች መጀመር




የሚኒሶታ የ EHDI ፕሮግራም ድረገጽ ለወላጆች፣ አቅራቢዎች እና ሌሎች ባለሙያዎች መርጃዎችን ያቀርባል። ወላጆች ስለ EHDI ሂደት ማወቅ፣ በጨቅላ ህጻን የመስማት ችሎታ መጠኖች ምዘና በኩል እንዲመሯቸው የሚያግዙ ቁሳቁሶችን ማግኘት፣ የቅድመ ጣልቃገብነት መርጃዎች እና በአካባቢያቸው የጆሮ ልዩ ባለሙያዎችን እና የትምህርት መርጃዎችን ማግኘት ይችላሉ። እንዲሁም ጣቢያው ወላጆች በአካባቢያቸው ከሚገኙ የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ድጋፍ ስርዓቶች ጋር እንዲገናኙ ለማገዝ መረጃ ይሰጣል።

### ይህን ያውቁ ኖሯል?

በየዓመቱ ፣ በሚኒሶታ ውስጥ

**ከ300 ህጻናትውስጥ 1 ልጅ**

**በአራስ ህጻን**

**የመስማት ችሎታ ማጣሪያ አማካኝነት የመስማት ችሎታ ምርመራ ሊገኝ**

**በሚችለው ከመደበኛ መጠን ውጭ በሆነ የመስማት ችሎታ ደረጃዎች ይወለዳል።**



### ስለ ማጣሪያ ምርመራተጨማሪ ጥያቄዎች አልዎት?

በ (800) 664-7772* ላይ ለአራስ ህጻን ማጣሪያ ፕሮግራም ለመደወል ነጻነት ይሰማዎ ወይም በሚከተለው ላይ በመስመር ላይ ይጎብኙን፡-
www.health.state.mn.us/newbornscreening or www.health.mn.gov/improveEhdi

*አስተርጓሚዎች ይገኛሉ

DEPARTMENT OF HEALTH

Rev: 2/2025 ID# 53323-AM

Minnesota Newborn Screening Program | www.health.state.mn.us/newbornscreening
P.O. Box 64899, St. Paul, MN 55164
ይህንን መረጃ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፡-
health.newbornscreening@state.mn.us ይገናኙ
ወይም ወደ (800) 664-7772 ይደውሉ *አስተርጓሚዎች አሉ